# ሞሄ አሳካህው !

# ዛሬም ዳግም ኮራን !

አቤ ፣ ምሩጽ ፣ ማሞ ኩራት ክብር ሲሆኑን
ሃይሌ ቀናኒሳ ደራርቱ ጀግንነቱን ሲያቀባብሉን
ባይሰጡ ባያወረሱን የአጭር ርቀት ሚስጥሩን
በረጅም ርቀት በማራቶን ተወስነን
ትንፋሽ ውጠን ሳንደፍረው መክረማችን
ጊዜን መግፋቱ ግድ ነበር አጭር ርቀትን ሸሽተን

ዳሩ ግና . ...
ረጅሙን ስንጓዝ በኩራት አጭሩን ትተን
አጭር ሮጠን ድል መንሳት ባይለምድብን
ሩቅ አስበን በአጭሩ እንዳንቀር ሙሄ ለእኛ ተላከልን
"ምን ሲባል! "ብሎ አንበሳው ከተፍ አለልን
ትንታጉ ወጣት መሃመድ አማን !

አንበሳው መሃመድ ...

" ገስግስ " እንዳልክ ካች አምና ነክሰህ ጥርሰህን
ሞስኮ ላይ ይህው ደረስክልን
ያልተደፈረ የአጭር ርቀትን ደፈርክልን
አሸንፈህ አሳካህው ! ዳግም ሮጠህ አኮራህን !




ትንታጉ ሙሄ ...

ዳግም ክብር ኩራት ሆንከን
አስደሰትክ አስፈነጠዝከን
እንኳን ደስ አለህ ! ደስ አለን !
ትናንት በጥሩየ ዛሬ ባንተ በቁርጡ ቀን ልጃቸን!
ከፍ አለ በሞስኮ ምድር ባንዴራችን!
ሰንደቃችን ዛሬም በአለም ፊት አውለበለብን!
ሞሄ አሳካህው ! ዛሬም ዳግም ኮራን !
ክብር ይገባሃል አንበሳችን !
ኩራት ነህና ለሃገራችን !
ይድረሰህ ፍቅር፣ ክብር ፣ ሞገሳችን !
እንዎድሃለን ! እናመሰግንህማለን !
ዛሬም ድል ለአትሌቶቻችን !







ነቢዩ ሲራክ
ከሳውዲ አረቢያ